## በሌቦቹ መንደር

የትግራይ ህዝብ ወዶ፣ ወገኖቼ ብሎ የወያኔ ትግሬን ወንጀል ይሁን ብሎም ይሁን ተገዶና ፈርቶ በማናውቀው መንገድ ወያኔን ደግፎ ለውጡን ተቃውሞ ሰልፍ መውጣቱ የኢትዮጵያን ህዝብእጅግ አስደምሞታል። የሰውን ልብ መርማሪው አምላክ ብቻ ነው። የሰው ልጅ ግን ከሚያየውና ከሚሰማው ተነስቶ ይፈርዳል።

በትግራይ ወያኔ ረዥም እጅ አገር ሲናጥ፣ ዘግናኝና ለጆሮ የሚቀፍ ትልልቅ ወንጀል ሲፈፀም፣ የሰው ልጅ ያለጥፋቱ ሲገደል፣ በእሳት ሲቃጠል፣ ሴቶች ሲደፈሩ፣ ወንዶች ሲኮላሹ፣ እግር ሲቆረጥ፣ ብልት ሲሰለብ፣ ወጣት ሴቶች እንዳይወልዱ ማምከኛ መርፌ ሲወጉ፣ አገር ሲዘረፍ፣ ተራራ ሲሰረቅ፣ መስኪድና ቤተክርስቲያን ሲቃጠል፣ 27 አመት ሙሉ ተሳስቶ እንኳን ሰልፍ ያልወጣ ህዝብ ዛሬ እርሙን ሰልፍ ቢወጣ ወንጀለኞቹን አትንኩብን ማለቱ አጠያያቂ ነው።

የፈለገ ቢሆን ለሚያልፍ ቀን ከውነት ጋር ቆመው የሚመጣውን ለመቀበል መዘጋጀት ነበረባቸው ብየ ስላሰብኩ፣ እኔም በመገናኛ ብዙሀን እንደሚታየውና እንደሚሰማው ሁሉ ቅሬታየን በዚህ መልክ ገልጫለሁ።

በሌቦቹ ክልል - በሌቦቹ መንደር

እውነት አፈር በላች - ሸፍጥ ቆመ በእግር

መሸገዋል አሉ - ድጋፍም አላቸው

ነውራቸውን ደፍሮ - ማን በነገራቸው

ባይተዋር አድርገው - ዜጋውን በአገሩ

ከፋፍለው ሲያባሉ - አምላክን ሳይፈሩ

ሌብነት ስራ ነው - ብለው ሲያስተምሩ

ሲገድሉ ሲዘርፉ - ህዝብ ሲያሸብሩ

ተጣርተን ነበረ - ደግመን ደጋግመን

የትግራይ ህዝብ - ሰምቶ እንዲደግፈን

በደሉ አንገሽግሾት - እንዲደርስልን

ጆሮ ዳባ ልበስ - እንዳላለን ዛሬ

ተሰለፈ ሰማን - ቆሞ ለነ አጅሬ

በእጅጉ አስደመሙን - ከእውነት ሲሸሹ

ማተብ የሚባል ቃል - በኀጥ ሲያበላሹ

ከወንጀለኞቹ - ከሌቦቹ መንደር

ብዙ ደም እንዳለ - ይታወጅ ይነገር

የአሁኑ ይባስ ነው - ወይ ነዶ ወይ ነዶ!

ወጥቶ ተሰለፈ - ትግራይ አቋም ወስዶ

ሰቅጣጭ ወንጀለኛ - በኀጥ ከደገፉ

የትግራይን ምድር - የሌቦቹ መንደር - አርገዋት አረፉ።